እያደረጉ ሲሆን፣ በአንደኛው ግለሰብ ላይ በብር 72,716.33 እምነት የማጉደል ክስ ተመስርቶ ጉዳዩ በፍ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛል።

- እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦች ያጉደሉትን የመንግሥት ገንዘብ እንዲመልሱ በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት እስከ አሁን ድረስ ብር 10,500 ገቢ ተደርጓል።

- ከሰኔ 30/1996 ዓ.ም በፊት የተለያዩ ግለሰቦች የመ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩበት ወቅት ያጉደሉትን የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፍሉ በጠቅላላ በብር 69,184.92 ላይ መ/ቤቱ ክስ መስርቶ ጉዳዩ በፍ/ቤት ክትትል እየተደረገበት ይገኛል።

- መ/ቤቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው ሁለት ግለሰቦች በተለያዩ ፍ/ቤቶች ያቀረቡት የብር 150,000 እና የብር 102,000 ክስ በተደረገው ክትትል ባለፈው ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለመጀመሪያው ክስ ፍርድ ቤቱ መድን ድርጅት በገባው ዋስትና መሠረት ብር 10,000 ይክፈል በማለት መ/ቤቱን በነጻ አሰናብቷል። እንዲሁም ከ102,000 ብር ክስ ውስጥ ደግሞ መ/ቤቱ ብር 29,520 እንዲከፍል ተወስኗል። እንዲሁም በሐረር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበ የብር 116,000 (አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺህ ብር) የጉዳት ካሣ ይከፈለኝ ክስ ተዘግቶ መ/ቤቱ በነፃ ተሰናብቷል።

- የመ/ቤቱ ሠራተኞች ያጎደሉትን ብር 9,448.76 እንዲከፍሉ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት መ/ቤቱ ክስ መስርቶባቸው እስካሁን በተደረገው ክትትል ፍ/ቤቱ ባደረገው የማጣራትና የዳኝነት ውሳኔ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ፍርድ ቤቱ ወስኖ ፋይሉ ተዘግቷል።

- የቦሌ ማተሚያ ድርጅት በ1989 ዓ.ም መ/ቤቱ ጋር በገባው ውል መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባውን ብር 708.75 እንዲከፈለው ኅዳር 14 ቀን 1997 ዓ.ም በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ እስከዛሬ ክፍያውን ባለመጠየቁ ጥፋቱ የድርጅቱ በመሆኑ የጠየቀውን ወለድና ሌሎች ወጪዎች ሳይጨምር ዋናውን ገንዘብ ብቻ መ/ቤቱ እንዲከፍለው ተደርጓል።

መ/ቤቱን ሲለቁ 3 በዲስፕሊን ጉድለት ከሥራ ተሰናብተዋል፡፡ እንዲሁም 15 በሞት ሲለዩ የ53 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር የተፈጸመ ሲሆን 3 ሠራተኞች በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ስራ ተመልሰዋል፡፡ በሌላ በኩል ከ2,570 የኮንትራት ሠራተኞች ላይ 4,422 ሲቀጠሩ እነዚህም 4,190 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች 1 የጥበቃ፣ 31 ሹፌሮች፣ 3 የሂሳብ ሠራተኛ፣ 77 የዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች፣ 4 የኤዲቲንግ ኮዲንግ ሠራተኞች 85 ጀማሪ ስታቲስቲሽያን፣27 የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎችና የ3 ፕሮግራመር ሠራተኞች ናቸው፡፡ በተመሣሣይ ወቅት ከመ/ቤቱ በጠቅላላው 4,050 የኮንትራት ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ተሰናብተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ 2,944 የኮንትራት ሠራተኞች በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህም መሠረት በዕቅድ ዘመኑ ዘጠኛ ወር መጨረሻ ላይ ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል 4,491 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,547 ቋሚና 2,944 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 2 <u>የሰዉ ኃይል ሁኔታ</u>

| ተ.ቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,535 | 2,570 | 4,105 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 53 | 4,422 | 4,475 |
| 3 | በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ሥራ የተመለሰ | 3 | - | 3 |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (29) | (4,048) | (4,077) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (15) | - | (15) |
| 6 | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | 1,547 | 2,944 | 4,491 |

የቋሚ ሠራተኞች ሁኔታ በአገልግሎት ዓይነት ሲተነተን ፕሮፌሽናል 148 ፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል 831፣ ሲሆኑ 568 የአስተዳደር የጽህፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው፡፡

በ1997 የዕቅድ ዘመን ዘጠኝ ወራት መጨረሻ ላይ ያሉት የመ/ቤቱ ቋሚና የኮንትራት ሠራተኞችን ሁኔታ በሥራ መደብ በመለየት በሚከተለው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

* መ/ቤቱ የተጠቀመባቸው የስልክ የመብራትና የውሃ ፍጆታ የክፍያ ጥያቄ ቢሉን በማየት አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ ለክፍያ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

* በመ/ቤቱ ከአገልግሎት ውጪ የነገሩ ተሽከርካሪዎችን እንዲወገዱ በተወሰነው መሠረት ጨረታ ወጥቶና ሺያጩ ተፈጽሞ ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ ሆኗል፡፡

* ከውጪ በዕርዳታ የመጡ ኮምፒውተሮች ከግምሩክ ወደ መ/ቤቱ እንዲገቡ ተደርጎ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

13.3.2 <u>ትራንስፖርትና ጥገና ክፍል</u>

* በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚገኙ 206 የመስክና የሰርቪስ ተሽከርካሪዎች በደንበኞች ጋራዥ ተጠግነው ለሥምሪት ብቁ የተደረጉ ሲሆን፣ 30 ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ጋራዥ ጥገና ተደርጎላቸው፡፡ እንዲሁም የዋናው መ/ቤት መካኒኮች ወደቅ/ጽ/ቤቶች በመንቀሳቀስ 3 የቆሙ ተሽከርካሪዎችን በመጠገን ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል፡፡

* አደጋ ለደረሰባቸው የመ/ቤቱ 21 ተሽከርካሪዎች በኢንሹራንስ ተሠርተው ወደ ምድብ ቦታቸው የተሰማሩ ሲሆን፣ 3 ተሽከርካሪዎች በኢንሹራንስ ጋራዥ በጥገና ላይ ይገኛሉ፡፡ ሁሉም የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ደህንነት ምርመራ ተደርጎላቸው ቴክኒካዊ ብቃታቸው ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

13.3.3 <u>ሕትመት ዋና ክፍል</u>

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ድረስ በጠቅላላው 273,834 ጥራዝ ጠቅላላ የገጽ ብዛታቸው 9,115,394 የሆኑ የሕትመት ሥራዎች ለመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

